# ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)
# የ 2018-2019 ካፍቴሪያ ዜና እና የኤለመንተሪ ት/ቤት ምግቦች መረጃ

የምግብና ሥርአተምግብ አገልግሎት በየዓመቱ 15 ሚሊዮን ምግቦችን ያገለግላል። ለተማሪዎች ጤናማ የሆነ የምግብ ምርጫን እንደግፋለን እናም ተማሪዎች ጠቀሜታ ያላቸው ምግቦችን በደስታ እንዲመገቡ ለማድረግ በተከታታይ አዳዲስ መንገዶችን እንቀይሳለን። የበለጠ መረጃ ለማግኘት በዚህ ድረ-ገጽ ይጎብኙን:- http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/foodserv/menus/cafemenus.aspx

ካፍቴሪያው በኮምፒውተር ለአከፋፈል የሚያመች ቀጣይነት ያለው የካሽ ረጂስተር ሲስተም ይኖረዋል። በካፍቴሪያው አካውንት ገንዘብ ተቀማጭ ማድረግ ልጅ በየቀኑ ገንዘብ ይዞ/ይዛ መጓዝን ያስወግዳል። አካውንቱን ለመጠቀም ተማሪዎች የግላቸውን መለያ ቁጥር (PIN) ማስገባት አለባቸው። ወደ ነበሩበት ት/ቤት የሚመለሱ ተማሪዎች ያኑ ተመሣሣይ የመለያ ቁጥር (PIN) ይጠቀማሉ። አዳዲስ ተማሪዎች በት/ቤት የመጀመሪያው ቀን የራሳቸውን መለያ ቁጥር (PIN) ያገኛሉ። ካለፈው ዓመት በተማሪው(ዋ) አካውንት የቀረ ማንኛውንም ገንዘብ በዚህ ዓመት ለመጠቀም ይቻላል። ት/ቤት ከመጀመሩ አስቀድሞ በተማሪ አካውንት ላይ የቅድሚያ ክፍያ ለመክፈል ይቻላል።

ቅድሚያ ክፍያ ለመፈጸም:-
ኦንላይን አገልግሎት በመጠቀም በክሬዲት ካርድ ቅድሚያ ክፍያ ለመፈጸም MySchoolBucks.com ይጠቀሙ። ወላጆች የምግብ አካውንቶቻቸውን ቀሪ ሂሳብ ለማየት/ለማረጋገጥ፣ ተደጋጋሚ ክፍያዎችን ለመፈጸም እና ሌሎችንም መረጃዎች ለማግኘት ይችላሉ። ለመመዝገብ MySchoolBucks.com ይክፈቱ:-

ከዚህ በታች ያለውን ቅጽ/ፎርም ሞልተው ለካፍቴሪያ የሚከፈል የሚል ቼክ ይጨምሩበት። ከዚህ በታች ያለውን የቼክ ክፍያ/ተቀባይነት ፖሊሲ ይመልከቱ።

ተመላሽ ክፍያ ለመጠየቅ ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ለማይቀጥል ተማሪ ቀሪ ሂሳብ ካለ እንዲዛወር DFNSHelpDesk@mcpsmd.org በኢ-ሜይል ይጠይቁ።

### የቼክ አከፋፈል/ተቀባይነት ፖሊሲ

ለት/ቤት ምግብ በሚከፈሉ ቼኮች ላይ:- ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ እና የተማሪ PIN ቁጥር መገለጽ አለበት። ተመላሽ ቼኮች ለተከሰተው ወጭ ማካካሻ እንዲውሉ ይዳረጋሉ። እንደዚሁም የሜሪላንድ ስቴት (Maryland State) በኤሌክትሮኒክ ዴቢት ወይም የወረቀት ድራፍት የሚከፈል የ$25 ክፍያ ለዛው አካውንት ፈቅዷል። የእርስዎ የቼክ ክፍያ እነኝህን መመሪያዎች መቀበልዎን ያረጋግጣል። ስለ እኛ የቼክ ክፍያ/አቀባበል ፖሊሲ ጥያቄዎች ካላችሁ እባክዎን CHECKredi at 1-800-239-1222 ይደውሉ።

| የኤለመንታሪ ት/ቤት ምግብ ዋጋዎች | |
|---|---|
| የምሳ ምግብ | $2.55 |
| ቅናሽ-ዋጋ የምሳ ምግብ | $0.40 |
| የቁርስ ምግብ | $1.30 |
| ቅናሽ-ዋጋ የቁርስ ምግብ | $0.00 |
| ወተት | $0.60 |

### የነፃ እና የቅናሽ-ዋጋ ምግብ ማመልከቻ

የፌደራል የገቢ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ቤተሰቦች ለነፃ ወይም የቅናሽ ዋጋ ምግብ ጥቅሞችን ለማግኘት ብቃት ይኖራቸዋል። ማንኛውም ልጅ የነፃ ወይም የቅናሽ ዋጋ ምግብ እንደሚያገኝ ሚስጥራዊነቱ እንዲጠበቅ ሁሉም ልጆች PIN ቁጥር ይጠቀማሉ። በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ ለሁሉም ተማሪዎች ከሚሰጣቸው የኢንፎርሜሽን ፓኬጅ ጋር ለምግብ ተጠቃሚነት የተዘጋጁ ማመልከቻዎች ወደቤት ይላካሉ። በዚህ ዓመት አዲስ:- የሚያመለክቱ ቤተሰቦች በ MySchoolApps.com ድረ-ገጽ ማመልከት ይችላሉ። በአንድ ቤተሰብ ለሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ አንድ ማመልከቻ ብቻ ያስፈልጋል። በዚህ የትምህርት ዓመት ድጋፍ የሚጠይቁ ቤተሰቦች አዲስ ማመልከቻ መሙላት አለባቸው። በድረ-ገጽ ከሆነ ያመለከቱት፣ እባክዎን የወረቀት ማመልከቻ አያቅርቡ።

ከቁርስ እና ምሳ በተጨማሪ ለመግዛት ምግብ እና መጠጦች ይገኛሉ።

በተማሪዎ ት/ቤት ካፍቴሪያ la carte items/ብቻቸውን የሚታዘዙ እና የሚከፈልባቸው በየአይነቱ ይገኛል። ለሽያጭ የሚቀርቡት ምግቦች በጠቅላላ የ JPG-RA መስፈርት ያሚሉ ናቸው። መልካም ጤንነት/ደህንነት:- የአካላዊ እና የምግብ ጤንነት በእያንዳንዱ ት/ቤት የተወሰኑ ነገሮች/items ይለያያሉ።

በልጅዎ ት/ቤት ስለሚገኙ ዝርዝር ነገሮች ኢንፎርሜሽን ወይም la carte items/ብቻቸውን የሚታዘዙ እና የሚከፈልባቸው ምግቦች ግዢን ውስን ለማድረግ፣ እባክዎ የት/ቤትዎን ካፍቴሪያ ማናጀር ያነጋግሩ።

---

### የቅድሚያ ክፍያ ቅጽ/ፎርም

እባክዎ የክፍያ ቼክ ላይ የት/ቤቱን ስም ጨምረው ለካፍቴሪያ የሚከፈል ተብሎ ይጻፍ። ለት/ቤት ምግቦች ለመክፈል የሚጠቀሙባቸው ቼኮች ላይ አድራሻ እና የስልክ ቁጥር እንዲኖርባቸው ያስፈልጋል። እባክዎ የልጅዎን የመጀመሪያ ስም፣ የአያት ስም እና PIN ቁጥር በቼኩ ፊት ለፊት ላይ ያስቀምጡ። ይህ ቼክ ለካፍቴሪያ ክፍያ/ግዢ ብቻ ነው። እባክዎን እያንዳንዱን ተማሪ በተለይ በመመዝገብ ክፍያውን ለካፍቴሪያ ማናጀር ያቅርቡ። እናመሰግናለን!

የተማሪ ስም ______________________ PIN ________ የክፍያ መጠን $ ________

የተማሪ ስም ______________________ PIN ________ የክፍያ መጠን $ ________

የተማሪ ስም ______________________ PIN ________ የክፍያ መጠን $ ________

የወላጆች/የሞግዚቶች ስም ______________________